# የኢሚግሬሽን መመሪያ ተደጋጋሚ ጥያቄዎች ማጠቃለያ

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ዘር፣ብሔር፣ወይም የኢሚግሬሽን ሁኔታን ከግምት ሳያስገባ በቦታው ውስጥ የሚኖሩትን ተማሪዎች በሙሉ ማስተማር ሕገ መንግሥታዊ ግዴታውን መሆኑን ያውቃል። ከዋሽንግተን ስቴት የህዝብ ትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (OSPI) የተሰጠውን ትእዛዝ እና መመሪያ መሰረት በማድረግ፣ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ቤት መሪዎች ከኢሚግሬሽን አስከባሪ ባለስልጣናት እና ከቤተሰቦች ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተ በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ ይህንን ሰነድ አዘጋጅቷል።

**የመመሪያ መርሆዎች**

1. **ወደ የህዝብ ትምህርቶች መግባት።**የ*Plyler v. Doe* የዩናይትድ ስቴትስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ መሰረት በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ የሚኖሩ ሁሉም ልጆች የኢሚግሬሽን ሁኔታቸው ምንም ይሁን ምን በሕዝብ ትምህርት ቤቶች መማር ሕገ መንግሥታዊ መብታቸው መሆኑን ይገልጻል።

   ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን ወይም ቤተሰቦቻቸውን የስደት ሁኔታ መረጃ እንዲሰጡ አይጠይቅም ወይም አይዝም፣እና ሰራተኞቹ በሕግ ካልተፈለገ በስተቀር ማንኛውንም የተማሪ መረጃ ይፋ አያደርጉም።

2. **ደህንነታቸው የተጠበቁ እና ተቀባይ የሆኑ ትምህርት ቤቶች።**የሲያትል የትምህርት ቦርድ ውሳኔ ቁጥር 2016/17-12 ዲስትሪክቱ ዘር፣ሀይማኖት፣የትውልድ ሀገር፣ወይም የኢሚግሬሽን ሁኔታ ከግምት ሳያስገባ ለሁሉም ተማሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ፣ተቀባይ እና አካታች ትምህርት ቤቶች እንዲያቀርብ ያረጋግጣል።ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በየስደተኞች ሁኔታ ላይ ተመስርተው ተማሪዎችን ወደ ትምህርት ቤት እንዳይሄዱ የሚያበረታታ ወይም ወደ መገለል የሚያደርስ እርምጃ አይወስድም።

3. **የዋሽንግተን የስራ ህግን መከተል።**የስቴት ህግ፣RCW 43.10.310 የህዝብ ትምህርት ቤቶች ዲስትሪክቶች ከፌደራል እና ከክልል ህግ ጋር በተጣጣመ መልኩ በትምህርት ቤቶች ውስጥ የኢሚግሬሽን አስፈጻሚዎችን የሚገድቡ ፖሊሲዎችን እና ሂደቶችን እንዲያወጡ ያዛል።ይህ የኢሚግሬሽን ወይም የዜግነት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን ትምህርት ቤቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ እና ለሁሉም የዋሽንግተን ነዋሪዎች ተደራሽ መሆናቸውን ያረጋግጣል።

4. **የተማሪዎችን ሚስጥራዊነት መጠበቅ።**ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር፣የቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና ግላዊነት ህግ ("FERPA") የተማሪውን ወላጅ/አሳዳጊ የጽሁፍ ፈቃድ ሳያገኙ የተማሪን መለያ መረጃ ይፋ ማድረግን ይከለክላል።

   በተጨማሪም OSPI የዋሽንግተን የህዝብ ትምህርት ቤቶች የተማሪ መረጃን ለመለዋወጥ ከፌደራል የስደተኞች ባለስልጣናት ጋር ግንኙነት መፍጠር እንደሌለባቸው ይመክራል።

5. **የዋሽንግተን ስቴት አድሎአዊ ያልሆኑ ህጎች።** የዋሽንግተን ስቴት ሕገ መንግሥት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በስቴቱ ውስጥ ለሚኖሩ ልጆች ሁሉ ከአድልዎ ነፃ በሆነ መንገድ ትምህርት እንዲሰጡ ያስገድዳል።የስቴት ህግ በተጨማሪም የትምህርት ዲስትሪክቶች በዘር፣በቀለም፣በብሄር፣በዜግነት ወይም በኢሚግሬሽን ሁኔታ አድልዎ እንዳይፈጽሙ ይከለክላል።

6. **የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የጎብኚ ፖሊሲዎች።**[የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የቦርድ ፖሊሲ ቁጥር 4200፣](#)የትምህርት ቤቶች ጉብኝቶች እና ደህንነቱ የተጠበቀ እና ሥርዓታማ አካባቢዎችን መጠበቅ፣የሚያስከትሉትን የትምህርት ፕሮግራም መቋረጥ አነስተኛ ከሆነ እና ከዲስትሪክቱ ሂደቶች ጋር የሚጣጣሙ ከሆነ የትምህርት ቤቶች ጉብኝት ይፈቀዳል።ያልተፈቀደላቸው ሰዎች በዲስትሪክቱ ንብረት ላይ መገኘት ጥሰት እንደፈጸሙ ይቆጠራሉ።

---

ወደ ትምህርት ቤቶች የመግባት ጥያቄዎች

---

### *የፌደራል ኤጀንሲዎች በትምህርት ቤቶች ውስጥ የህግ ማስፈጸሚያ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ይፈቀድላቸዋል?*

በጥር 21, 2025 የዩኤስ የሀገር ውስጥ ደህንነት ክፍል (“DHS”) ትምህርት ቤቶችን በአጠቃላይ የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ እርምጃ የማይከሰትባቸውን “ስሱ አካባቢዎች(“sensitive locations)” ብሎ በ መሰየም የረዥም ጊዜ የፌደራል ፖሊሲውን ሽሯል።ሆኖም የኢሚግሬሽን እና የጉምሩክ ማስፈጸሚያ (“ICE”) ወይም ሌላ ማንኛውም የፌደራል ኤጀንሲ ለህግ ማስፈጸሚያ ዓላማዎች ትምህርት ቤት መግባት ከፈለገ ሕገ መንግሥታዊ ጥበቃዎች አሁንም ተፈጻሚ ይሆናሉ።በዚህ ምክንያት፣ማንኛውም የICE ጥያቄዎች በተገቢው ህጋዊ ባለስልጣን መደገፋቸውን ለማረጋገጥ ሁሉም የትምህርት ቤት ሰራተኞች በሱፐርኢንቴንደንት አሰራር 4310SP.B የተዘረዘሩትን ፕሮቶኮሎች መከተል ወሳኝ ነው።

### *ICE ወደ ትምህርት ቤት ግቢ ለህግ የማስፈጸም ዓላማ ከመጣ ትምህርት ቤቶች ምን ማድረግ አለባቸው?*

የት/ቤት ሰራተኞች [በሱፐርኢንቴንደንት አሰራር 4310SP.B](#) እና በተዛመደ አጠቃላይ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን ፕሮቶኮሎች መከተል አለባቸው።ይህም ወደ የት/ቤት መገልገያዎች ወድያውኑ እንዳይገቡ መከልከል፣ርእሰ መምህሩን ማሳወቅ እና ለመግባት ከመፍቀድዎ ወይም ማንኛውንም መረጃ ይፋ ከማድረግዎ በፊት ጥያቄውን እንዲገመገም ወደ የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች አጠቃላይ አማካሪ ቢሮ ማስተላለፍን ይጨምራል።

### *የፌደራል የኢሚግሬሽን ባለስልጣን ምን አይነት ሰነድ ማቅረብ አለበት?*

መረጃ፣ተማሪዎችን ወይም የትምህርት ቤት መገልገያዎችን ለማግኘት የሚፈልጉ የፌዴራል የኢሚግሬሽን ባለስልጣናት ለጥያቄያቸው ህጋዊ ሰነድ ማቅረብ አለባቸው።እንዚህ ህጋዊ ሰነዶች የፍርድ ቤት ትዕዛዝ፣የፍርድ ቤት መጥሪያ ወይም የፍርድ ቤት ማዘዣ ሊያካትቱ ይችላሉ።የአጠቃላይ አማካሪ ጽሕፈት ቤት ጥያቄውን ከመመለሱ በፊት እነዚህን ሰነዶች ትክክለኛነት እና ገደብ መገምገም አለበት።የሆነ መኮንን እንደዚህ አይነት ሰነዶችን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ፣ወደ ትምህርት ቤቱ ግቢ እንዳገባ ይከለከላል።

### *የፍርድ ቤት ማዘዣ ለህግ አስከባሪ አካላት ወይም ባለስልጣኖች ሰፋ ያለ እና አጠቃላይ ትምህርት ቤቱን እንዲፈትሹ መፍቀድ ይችላል?*

የፍርድ ቤት ማዘዣው በሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተቀባይነት እንዲኖረው፣ማዘዣው በዳኛ መፈረም፣ የሚፈጸመውን ተግባር ዓላማ መግለጽ፣የሚፈለግ(ለጉ) ቦታ(ዎች) መለየት እና መዳረሻ መሰጠት ያለበትን ሰው መጥቀስ አለበት።የትምህርት ቤት ሰራተኞች የማዘዣውን ትክክለኛነት ለመወሰን ከመሞከር መቆጠብ እና እንደዚህ ያሉ ሰነዶችን ለግምገማ ወደ አጠቃላይ አማካሪ ቢሮ መላክ አለባቸው።የፍርድ ቤት ማዘዣዎች እና የፍርድ ቤት ጥሪዎች በአብዛኛው የተገደቡ ስለሆኑ ሰራተኞች ግለሰቦችን ለማስገባት፣መረጃዎችን ወይም መዝገቦችን ለመስጠት የህግ አማካሪ የወሰነውን ብቻ መከተል አስፈላጊ ነው።

### *የትምህርት ቤቱ መሪ ከሌለ አሠራሩ ምንድን ነው?*

በትምህርት ሰዓት ወይም በትምህርት ቤት ስፖንሰር በሚደረጉ ዝግጅቶች፣ አስተዳዳሪ ወይም ተወካይ ሊኖር ይገባል።ርእሰመምህሩ የማይገኝ ከሆነ አስተዳዳሪ እና/ወይም ተወካይ የተቀመጡትን ሂደቶች መከተል አለባቸው።ት/ቤቶች ሁሉም ተወካዮች የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶችን አሰራር እንደሚያውቁ ማረጋገጥ አለባቸው።

### *ICE የፍርድ ቤት ማዘዣ፣መጥሪያ ወይም የፍርድ ቤት ትዕዛዝ ካሳየ እና በፍጥነት መግባት ከፈለገ ትምህርት ቤቶች ምን ምላሽ መስጠት አለባቸው??*

እነዚህ በአማካሪ በጥንቃቄ መገምገም የሚያስፈልጋቸው ህጋዊ ሰነዶች በመሆናቸው ትምህርት ቤቶች በሱፐርኢንቴንደንት አሰራር 4310SP.B ውስጥ ያሉትን ፕሮቶኮሎች በመከተል ተጨማሪ እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ከአጠቃላይ አማካሪ ቢሮ ፈቃድ ማግኘት አለባቸው።የአጠቃላይ ምክር አማካሪ በተቻለ ፍጥነት ግምገማውን ያካሂዳል።

### *የኢሚግሬሽን መኮንን ፕሮቶኮሉን ለማክበር ፈቃደኛ ካልሆነስ?*

የኢሚግሬሽን መኮንን ለመልቀቅ ወይም የርእሰመምህሩ መመሪያዎችን ለማክበር ፈቃደኛ ካልሆነ የትምህርት ቤት ሰራተኞች በማንኛውም የህግ አስፈጻሚ እርምጃ ላይ በአካል ጣልቃ ለመግባት መሞከር የለባቸውም። ርእሰመምህሩ ወይም ተወካዩ እንደ አስፈላጊነቱ ለተጨማሪ ድጋፍ ወደ ደህንነት ቢሮ (206-252-0707) መደወል እንዲሁም የ SPS 4-1-1 team (411@seattleschools.org) እና የክልል ዋና ዳይሬክተር ድጋፍ (REDSupport@seattleschools.org) ማግኘት አለባቸው።የት/ቤቶች ርእሰ መምህራን የ4-1-1 ሂደቱን ለመጀመር ወደ Dr. Marni Campbell ወይም Tyler Hamilton በTEAMs እንዲደውሉ ይበረታታሉ።

### *የ ICE ወኪል ያለ ህጋዊ ፍቃድ ወደ ህንፃው ከገባ ምን አይነት የደህንነት ሂደቶች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው?*

ማንኛውም ሰው-የ ICE ወኪልን ጨምሮ-ፈቃድ ለማግኘት የተቀመጠውን አሰራር ሳይከተል ወደ የሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ህንጻ ውስጥ ከገባ ህግ እንደ ተላላፈ ሊቆጠር ይችላል።በእነዚህ ሁኔታዎች ውስጥ ትምህርት ቤቱ ወደ መቆለፍ (lockdown) መግባት እና እርዳታ ለማግኘት ወዲያውኑ ወደ ደህንነት እና ጥበቃ መደወል አለበት።ከላይ እንደተብራራው፣ሰራተኞቹ በማንኛውም የህግ አስፈጻሚ እርምጃ ላይ አካላዊ ጣልቃ ለመግባት መሞከር የለባቸውም።

### *ሰራተኞች በየኢሚግሬሽን ህግ አስፈጻሚ እርምጃ ላይ ጣልቃ ቢገቡ ምን ይከሰታል?*

ትምህርት ቤቶች የፌደራል ህግ ማንኛውም ሰው በህገወጥ መንገድ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ ያሉ ግለሰቦችን ሆን ብሎ "መከላከል (“Harboring”)" የሚከለክል መሆኑን ማወቅ አለባቸው።መከላከል (“Harboring”) ማለት አንድን ግለሰብ እንዳይታወቅ መደበቅ ወይም መከላከል ወይም ግለሰቡ በህገ ወጥ መንገድ በአገር ውስጥ የሚቆይበትን ሁኔታ ለማመቻቸት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ማለት ነው።ነገር ግን፣የፌደራል ህግ ትምህርት ቤቶች በአደጋ ጊዜ የሚሰጡትን የድጋፍ አይነት አይከለክልም፣በኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ እርምጃ ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው ለታሰሩ ተማሪዎች ጭምር።

የትምህርት ቤት ሰራተኞች በተማሪዎች እና በቤተሰቦቻቸው፣በሰራተኞቻቸው እና በበጎ ፈቃደኞች ላይ በሚደረጉ የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ ተግባራት ላይ መሳተፍ ወይም መርዳት የተከለከሉ መሆናቸውን ያስተውሉ ።

### *ርእሰመምህሩ ለባለሥልጣኑ ምላሽ በሚሰጥበት ጊዜ ሌላ አስቸኳይ ጉዳይ ከተፈጠረ የት/ቤቱ ሠራተኞች ማንን ማግኘት አለባቸው?*

አስተዳዳሪዎች የደህንነት፣የዲሲፕሊን እና የተማሪ የጤና ጉዳዮችን የሚያካትቱ የአደጋ ጊዜ ሁኔታዎች አስመልክቶ የትምህርት ቤቱን ምላሽ የመቆጣጠር አጠቃላይ ሀላፊነት አለባቸው።ትምህርት ቤቶች በልዩ ሁኔታዎች ላይ ተመስርተው ለእንደዚህ አይነት ድንገተኛ አደጋዎች ምላሽ ለመስጠት መደበኛ ሂደታቸውን መከተል አለባቸው።ርእሰመምህሩ ለኢሚግሬሽን ባለስልጣን ጥያቄ ምላሽ ሲሰጥ ትምህርት ቤቶች አፋጣኝ ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ፣በ4-1-1 ሂደት መፍትሄ ያገኛል።

### *ICE ተማሪውን ለማግኘት ከጠየቀ የተማሪውን ወላጅ/አሳዳጊ ለማግኘት ትክክለኛው ጊዜ መቼ ነው?*

በሁሉም ሁኔታዎች፣የት/ቤቶች ርእሰ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በሚመለከት ማንኛውንም የኢሚግሬሽን ህግ አስፈጻሚ ድርጊቶች ለወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ ምክንያታዊ ጥረት ማድረግ አለባቸው።ይሁን እንጂ የዚህ ዓይነቱ ማስታወቂያ ጊዜ የሚወሰነው በጥያቄው ተፈጥሮ፣ስፋት እና ትክክለኛነት ላይ የተመሰረተ ነው።የፍርድ ቤቱ ማዘዣ አስቀድሞ ማሳወቅን ሊከለክል ስለሚችል የትምህርት ቤት ሰራተኞች ከጠቅላላ አማካሪ ቢሮ ጋር በየሁኔታው ማማከር አለባቸው።

የኢሚግሬሽን ባለስልጣን የተማሪን መዝገብ ወይም መረጃ ከፈለገ እና የማዘዣ ወረቀት ካቀረበ ሰራተኞቹ ለግምገማ ወደ አጠቃላይ አማካሪ ቢሮ መላክ አለባቸው።ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር፣FERPA ትምህርት ቤቶች መረጃውን ይፋ ከማድረጋቸው በፊት ትዕዛዙን ወይም መጥሪያውን የተማሪውን ወላጅ/አሳዳጊ ለማሳወቅ ምክንያታዊ ጥረት እንዲያደርጉ ይጠይቃል፣ይህም ወላጆች የመከላከያ እርምጃ እንዲፈልጉ ይስችላቸዋል።

---

## ከካምፓስ ውጪ እና ከትምህርት በኋላ ያሉ ዝግጅቶች

---

### *የኢሚግሬሽን ባለስልጣናት እንደ የትምህርት ቤት ዳንሶች ወይም የወላጅ ስብሰባዎች ያሉ የምሽት ዝግጅቶችን ለማግኘት ከሞከሩ ትምህርት ቤቶች ምን ማድረግ አለባቸው?*

ለሕዝብ ክፍት ባልሆኑ የከትምህርት በኋላ ዝግጅቶች፣ሰራተኞቹ ተመሳሳይ ፕሮቶኮሎችን መከተላቸውን መቀጠል አለባቸው እና ያለ ህጋዊ ግምገማ እና ጥያቄውን ተቀባይነት ያላገኘ ማንኛውም የኢሚግሬሽን ባለስልጣን መግባት የለበትም።

### *በመስክ ጉዞዎች እና ሌሎች ከትምህት ቤቶች ግቢ ውጭ፣በትምህርት ቤት ስፖንሰር በሚደረጉ ዝግጅቶች ላይ ምን ፕሮቶኮሎች ተፈጻሚ ይሆናሉ?*

ተማሪዎች በትምህርት ቤት-ስፖንሰር በሚደረጉ የመስክ ጉዞዎች፣ከግቢ ውጭ ዝግጅቶች በሚሆኑበት ጊዜ ተማሪዎቹ በሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ቁጥጥር ውስጥ ናቸው።እነዚህን ከካምፓስ ውጭ ያሉ ቦታዎች ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ባይቆጣጠራቸውም፣[የሱፐርኢንቴንደንት አሰራ 4310SP.B] እና በ *loco parentis* ያሉትን መርሆች መተግበራቸውን ይቀጥላሉ።ሰራተኞ ተማሪዎችን ለማንኛውም ያልተፈቀደ ግለሰብ መልቀቅ የለባቸውም እና ተገቢውን የህግ ግምገማ እና ማፅደቅን በተመለከተ በሂደቱ ውስጥ የተዘረዘሩትን ሌሎች እርምጃዎች መከተል አለባቸው።

---

### *ICE ተማሪው በትምህርት ቤት መኖሩን ከጠየቀ ትምህርት ቤቶች እንዴት ምላሽ መስጠት አለባቸው?*

የተማሪ መረጃ በ FERPA የተጠበቀ ነው እና ባለስልጣኑ መረጃውን ለማግኘት ትክክለኛ ህጋዊ ስልጣን ከሌለው በስተቀር መሰጠት የለበትም።በዚህ ምክንያት ሰራተኞቹ የተማሪ ማንኛውንም መረጃ ከማቅረባቸው በፊት ከሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች አጠቃላይ አማካሪ ጋር መማከር አለባቸው።

### *የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ስለየተማሪዎች የስደት ሁኔታ መረጃ መሰብሰብ ወይም መጠየቅ አለባቸው?*

አይችሉም።በ *Plyler v. Doe* መሰረት የK-12 ትምህርት ቤቶች የማህበራዊ ዋስትና ቁጥሮችን ጨምሮ ስለተማሪ የኢሚግሬሽን ሁኔታ መረጃ እንዲሰበስቡ በፌደራል ህግ አይገደዱም እና  የተማሪ ምዝገባን ሊያደናቅፍ ስለሚችል ሰራተኞቹ መረጃ ከመጠየቅ መቆጠብ አለባቸው።

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች ወይም ቤተሰቦቻቸው ስለ የስደት ሁኔታቸው መረጃ ለትምህርት ቤቱ ሰራተኞች እንዲሰጡ አይፈልግም።የትምህርት ቤት ሰራተኞች ስለስደት ሁኔት ተማሪዎችን ወይም ቤተሰቦቻቸውን ከመጠየቅ መቆጠብ አለባቸው፣እንዲሁም ተማሪዎች ወይም ቤተሰባቸው እንደዚህ ያለውን መረጃ እራሳቸውን ካሳወቁ ሪከርድ ከመያዝ መቆጠብ አለባቸው።

### *ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን የስደተኝነት ሁኔታ ለሌሎች የመንግስት ኤጀንሲዎች ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል?*

*ትምህርት ቤቶች የተማሪዎችን የስደተኝነት ሁኔታ ለሌሎች የመንግስት ኤጀንሲዎች ማሳወቅ ይጠበቅባቸዋል?* አይችሉም፣ የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች ተማሪውን ሰነድ እንደሌለው መረጃ ካገኙ፣ ለሌላ የመንግስት ኤጀንሲ ሪፖርት ለማድረግ ምንም መስፈርት የለም።ይህን ማድረግ   እነዚያን ተማሪዎች ተስፋ በማስቆረጥ ወይም የህዝብ ትምህርት እንዳይሰጡ በመከልከል *Plyler v. Doe* መጣስ ሊሆን ይችላል።

### *ትምህርት ቤቶች ስለ የተማሪዎች የስደተኝነት ሁኔታ መረጃ የሚጠይቅ ማዘዣ ወይም ለሌላ ጥያቄ  እንዴት ምላሽ መስጠት አለባቸው?*

ትምህርት ቤቶች ከፌዴራል የኢሚግሬሽን ባለስልጣናት የሚቀርቡትን ሁሉንም የፍርድ ቤት መጥሪያ እና ሌሎች የሪከርድ ጥያቄዎች ለሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች አጠቃላይ አማካሪ ቢሮ ለግምገማ መላክ አለባቸው።ትምህርት ቤቶች ያለ ህጋዊ እውቅና ማንኛውንም መረጃ ለግለሰቡ በቀጥታ መልቀቅ የለባቸውም።ት/ቤቶች ከተወሰኑ ሁኔታዎች በስተቀር፣FERPA ያለ ወላጅ ፈቃድ የተማሪዎችን መለያ መረጃዎችን ይፋ እንዳያረጉ ይከለክላል።FERPA የዳኛ ትእዛዝ ወይም በህጋዊ መንገድ የተሰጠ የፍርድ ቤት መጥሪያን ለማክበር የተማሪ መዝገቦችን መልቀቅ ቢፈቅድም፣እነዚህ ሰነዶች ይፋ ከመደረጋቸው በፊት ጥንቃቄ የተሞላበት የህግ ግምገማ ያስፈልጋቸዋል።

## አቴንዳንስ

### *ከየኢሚግሬሽን ስጋቶች ጋር በተያያዘ ከትምህርት ቤት መቅረት አስመክቶ ትምህርት ቤቶች እንዴት መስራት አለባቸው?*

ተማሪው ከየኢሜግሬሽን ሁኔታው ጋር በተገናኘ ጭንቀት ወይም ፍርሃት ከትምህርት ቤት ከቀረ፣እነዚህ ቀሪዎች በየደህንነት ስጋት ምድብ ውስጥ ስለሚመደቡ እንደ ምክንያታዊ ቀሪ ይቆጠራሉ።የአቴንዳንስ ባለሞያ በቀሪው ላይ EA ኮድ መጠቀም አለበት።ትምህርት ቤቶች ስለነዚህ ምክንያታዊ መቅረቶች ተለዋዋጭ መሆን አለባቸው፣ ከየትምህርት ቤቱ የጊዜ ሰሌዳ በፊትም ሆነ በኋላ።

የአቴንዳንስ ስፔሻሊስቶች ስለጉዳዩ መረጃ ይሰጣቸዋል እንዲሁም መቅረት ለሚቀጥሉ ተማሪዎች ቤተሰቦችን እንዴት ማነጋገር እንደሚችሉ መመሪያ ይሰጣቸዋል። ተጨማሪ መረጃ በየ OSPI መመሪያ Compulsory Attendance and Truancy Considerations በሚለው ርዕስ ስር እዚህ ተያይዞ ይገኛል።

## መረጃ መጋራት

### *አንድ ተማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ በ IEC ከተያዘ፣ከሰራተኞች እና ከማህበረሰባችን ድጋፍ ይኖረናል?*

አዎ።የእያንዳንዱ ቤተሰብ እና የትምህርት ቤት ማህበረሰብ ጉዳይ በ4-1-1 ሂደት በኩል ደረጃ በደረጃ መፍትሄ ያገኛል።ማንኛውም ምላሽ ባሉ በተወሰኑ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ይሆናል።

### *ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የእኔ ትምህርት ቤት ባይሆንም በትምህርት ቤቶቻችን ውስጥ ስላለው የኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ እንቅስቃሴ መረጃን ይጋራሉ?*

የ ICE ህግ አስፈጻሚ ድርጊቶች የተወሰኑ ግለሰቦችን ስለሚያካትቱ እና በትላልቅ ግንኙነቶች በ FERPA አንድምታ ሊኖራቸው ስለሚችሉ ወቅታዊ መረጃዎች በየ4-1-1 ሂደት ይቀርባሉ።

### *የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የማህበረሰብ አጋሮች ስለነዚህ ፕሮቶኮሎች እንዴት ይነገራቸዋል?*

ሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች በተቻለ መጠን የሲያትል የሕዝብ ትምህርት ቤቶች የግንኙነት ፕሮቶኮሎች እና ልምምዶች በመከተል በኮሙኒኬሽን ዲፓርትመንት በኩል ለማህበረሰብ አቀፍ ድርጅቶች እና አጋሮች ለመጋራት ይሰራል።በተጨማሪም፣ርእሰ መምህራን ማንኛውንም የመመሪያ ሰነዶች፣ማጠቃለያዎች እና በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችን ለማህበረሰብ አጋር ድርጅቶች ጋር ማጋራት ይችላሉ።

## የቤተሰብ ድጋፎች እና ጸጋዎች

***ትምህርት ቤቶች ወላጅ/አሳዳጊ እንደታሰሩ ካወቁ ምን ማድረግ አለባቸው?*** ትምህርት ቤቶች በማንኛውም የችግር ጊዜ ውስጥ እንደሚያደርጉት በኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ እርምጃ የተጎዱ ተማሪዎችን ለመደገፍ ንቁ እርምጃዎችን መውሰድ አለባቸው።ለምሳሌ፣አንድ ትምህርት ቤት አንድ ወላጅ/አሳዳጊ እንደታሰረ ከተረዳ፣የትምህርት ቤቱ ሰራተኞች በ PowerSchool ውስጥ የተዘረዘሩትን የተማሪውን የአደጋ ጊዜ ተጠሪ አድራሻ በማየት ተማሪው በትምህርት ቀን መጨረሻ ላይ ከመልቀቁ በፊት በቂ ክትትል እንዳለው ያረጋግጣል።ትምህርት ቤቶች አስፈላጊ ከሆነ የህግ ኣማካሪ እና/ወይም የደህንነት ባለሞያ ማነጋገር አለባቸው እንዲሁም በኢሚግሬሽን ማስፈጸሚያ ድርጊቶች የተጎዱ ተማሪዎችን ከአማካሪዎች፣ማህበራዊ ሰራተኞች እና ሌሎች የአእምሮ ጤና ድጋፎች ጋር እንደአግባቡ ማገናኘት አለባቸው።

***ትምህርት ቤቶች ስለ ICE ማስፈጸሚያ የሚጨነቁ ተማሪዎችን እና ቤተሰቦችን እንዴት መደገፍ ይችላሉ?*** የ *Plyler v. Doe* የጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ እና የሲያትል ትምህርት ቤት ቦርድ ውሳኔ ቁጥር 2016/17-12 መሰረት፣ሰራተኞቹ ሲያትል የህዝብ ትምህርት ቤቶች ዘርን፣ሃይማኖትን፣ብሄራዊ ማንነትን ወይም የኢሚግሬሽን ሁኔታን ሳይመለከቱ ለሁሉም ተማሪዎች ደህንነቱ የተጠበቀ፣እንግዳ ተቀባይ እና አካታች የትምህርት አካባቢ እንደሚሰጡ ማረጋገጥ አለባቸው።ሰራተኞች ከቤተሰቦች ጋር በሚገናኙበት ጊዜ፣በትምህርት ቤት ማህበረሰባቸው ውስጥ ባለማወቅ ፍርሃትን ከማባባስ ወይም በስደተኝነት ሁኔታ ላይ ተመስርተው ወደ ትምህርት እንዳይመጡ ከማድረግ መቆጠብ አለባቸው።

***ትምህርት ቤቶች የኢሚግሬሽን መርጃዎችን ለቤተሰቦች ማጋራት ይችላሉ?***
አዎ።ትምህርት ቤቶች እንደ አስፈላጊነቱ ተማሪዎችን እና ቤተሰቦቻቸውን ከማህበረሰብ ሀብቶች ጋር እንዲያገናኙ ይበረታታሉ።የስደተኛ ጉዳዮችን ውስብስብ ባህሪ ከግምት ውስጥ በማስገባት የትምህርት ቤት ሰራተኞች የህግ ምክር መስጠት የለባቸውም፣ ይልቁንም ተማሪዎች እና ቤተሰቦቻቸው ከኢሚግሬሽን ባለሙያዎች ህጋዊ ምክር እንዲያገኙ ማበረታታት አለባቸው።

***ቤተሰቦችን በንቃት ለመርዳት ትምህርት ቤቶች ሌላ ምን ማድረግ ይችላሉ?***
ትምህርት ቤቶች ስለ የቤተሰብ ችግር ሁኔታዎች እና ስለ የሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች ዝግጅት አስፈላጊነት፣ የኢሚግሬሽን ህግ አስፈጻሚዎች እርምጃዎችን ጨምሮ ለመላው የትምህርት ቤት ማህበረሰብ አጠቃላይ ማሳሰቢያዎችን ሊሰጡ ይችላሉ።እንደዚህ አይነት ግንኙነቶች በማህበረሰቡ ውስጥ አላስፈላጊ ሽብር እንዳይፈጥሩ እና የትኛውንም ቤተሰብ ወይም የቤተሰብ ቡድን እንዳይለዩ መጠንቀቅ አለባቸው።

ትምህርት ቤቶች ቤተሰቦች በድንገተኛ ሁኔታ ጊዜ ተማሪያቸውን የሚንከባከብ እና የሚያሳደግ እቅድ እንዲያዘጋጁ ሊጠቁሙ ይችላሉ።ሁሉም ቤተሰቦች በ PowerSchool ያለውን የአደጋ ጊዜ ተጠሪ እና አድራሻ መረጃ እንዲሁም ተማሪዎቻቸውን ለመውሰድ ፍቃድ ያላቸውን ሰዎች ወቅታዊ መሆኑን እንዲያረጋግጡ መበረታታት አለባቸው።

***ምን ሌሎች መርጃዎች ይገኛሉ?***
የሲያትል የስደተኞች ጉዳይ ጽሕፈት ቤት የሕግ ድጋፍ መርጃዎችን የመብትዎን ይወቁ መረጃ ጨምሮ፣የስደተኞች አገልግሎቶች እና ፕሮግራሞች የያዘ አገናኝ( links )አቅርቧል።

**አጠቅላይ አማካሪ ቢሮ:** (206) 252-0110 or legal@seattleschools.org

**4-1-1 Team**: 411@seattleschools.org or *via Teams to*: Dr. Marni Campbell or Tyler Hamilton

**የክልላዊ ሥራ አስፈፃሚ ድጋፍ:** REDSupport@seattleschools.org

**የደህንነት ቢሮ**: (206) 252-0707 Security_office@seattleschools.org